የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፵፬
አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 44
ADDIS ABABA–8th April 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፬/፲፱፻፺፭ ዓ.ም

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ያደረገውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ

አዋጅ ...................................... ገጽ ፩ ሺ ፩፻፴፱

## CONTENTS

Proclamation No. 324/2003

A Proclamation to Ratify the Investment Incentive Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the United States of America

Proclamtion ............................................ Page 2139

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፬/፲፱፻፺፭

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ከአሜሪካ መንግሥት ጋር ያደረገውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በአሜሪካ መንግሥት መካከል የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስምምነት ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱ ሥራ ላይ የሚውለው በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ስምምነቱ መጽደቁን የሚያረጋግጡ ሠነዶች ለአሜሪካ መንግሥት በዲፕሎማቲክ አካላት በኩል ከተላከ በኋላ እንደሚሆን በስምምነቱ ስለተገለጸ ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብልክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት ከዚሀ እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ከአሜሪካ መንግሥት ጋር የተደረገውን የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፬/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· **ስምምነቱ ስለመጽደቁ**

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአሜሪካ መንግሥታት መካከል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት በአዲስ አበባ ከተማ ፣ ጥቅምት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ.ም. የተፈረመው ስምምነት ጸድቋል ።

## PROCLAMATION No. 324/2003

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE INVESTMENT INCENTIVE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE UNITED STATES OF AMERICA

WHEREAS, an Investment Incentive Agreement between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the government of the United States of America is signed in Addis Ababa, in October 24, 2000.

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that it shall enter into force on the date the government of Ethiopia notifies the government of the United States of America of the ratification, through diplomatic channels;

WHEREAS, the House of the Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on 8th day of April, 2003.

NOW, THEREFORE, In accordance with Article 55 Sub-Article (1) and (12)of the Constitution of the Federal Democratice Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*
   This proclamation may be cited as "The Investment Incentive Agreement with the government of the United States of America Ratification Proclamation No. 324/2003."

2. *Ratification of the Agreement*
   The Investment Incentive Agreement signed in Addis Ababa on October 24, 2000 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and government of the United States of America is ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· <u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ኃላፊነት</u>

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ስምምነቱን በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ኃላፊነት ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከመጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

*አዲስ አበባ መጋቢት ፴ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም. ።*

*ግርማ ወልደጊዮርጊስ*
*የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*
*ፕሬዚዳንት*

3. *Responsibility of the Ethiopian Investment Authority*

The Ethiopian Investment Authority is hereby empowered to implement this Agreement.

4. *Effective Date*

This proclamation shall enter into force as of 8th day of April, 2003.

*Done at Addis Ababa, this 8th day of April, 2003.*

*GIRMA WOLDE GIORGIS*
*PRESIDENT OF THE FEDERAL*
*DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA*

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE